የሰ/መ/ቁ 49750

መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/01 የመዝናኛ ክበብ -

ጠበቃ አሰፋ ዝቅአርጋቸው ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ማስረሻ ሁሴን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ ክሳቸውም ሰኔ 01 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ ሁኖ ይዘቱም ባጭሩ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከነሐሴ 01 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ተቀጥረው በወር ደመወዝ ብር 314(ሦስት መቶ አስራ አራት) እየተከፈላቸው በመስራት ላይ እንዳሉ ያላግባብ ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም ከስራ የተሰናበቱ መሆኑን በመግለፅ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ለክሱ በሠጠው መልስ፤ ስንብቱ የተከናወነው ተጠሪ የድርጅቱን ትዕዛዝ ባለማክበራቸው ስለመሆኑ በመግለፅ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት አመልካች ድርጅት ለተጠሪ የስራ ስንብት፣ የካሣ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ እንዲከፍላቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥቅምት 06 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ የተሰናበቱት የአመልካችን ትዕዛዝ ሊያከብሩ ባለመቻላቸው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤት ለሕብረት ስምምነቱ አፈፃፀም የተዛባ ትርጉም በመስጠት ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ጥር 25 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃም የካቲት 09 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የአመልካች ሰራተኛ ሆነው በሚሰሩበት የስራ ሠዓት ወቅት አመልካች የድራፍት በርሜል እንዲረከቡ ትዕዛዝ ሲያስተላልፍላቸው ሊቀበሉ ያልቻሉ መሆኑ የስር ፍርድ ቤት አረጋግጦ ይህ

የተጠሪ ድርጊት ከስራ ለመሰናበት ሕጋዊ ምክንያት አይደለም ለማለት የቻለው በሕብረት ስምምነቱ እንደጥፋት ቢጠቀስም ሰራተኛው ትዕዛዙ ሕገ-ወጥ እስከሆነ ድረስ ለመቃወም የሚችል ስለመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13(2) ድንጋጌ መረዳት ይቻላል በሚል ነው፡፡ በእርግጥ አንድ ሰራተኛ በስራ ውሉ ላይ የተጣለውን ግዴታ የመወጣት ኃላፊነት ያለው ስለመሆኑ ይኸው የተጠቀሰው ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል በአዋጁ በአንቀጽ 27(1/ሸ) ድንጋጌ ሕጉ ካስቀመጣቸው በተጨማሪ በሕብረት ስምምነቱ ላይ ከስራ ሊያስባርሩ የሚችሉ ጥፋቶችን መወሰን እንደሚቻል ተመልክቷል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ተጠሪን ከስራ ሊያሰናብታቸው የቻለው በሕብረት ስምምነቱ መሆኑን በመጥቀስ የሚከራከር ሲሆን የህብረት ስምምነቱ አለመታዘዝ ከማስጠንቀቂያ በኋላ ከስራ ሊያስባርር እንደሚችል ተቀምጧል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህ የሕብረት ስምምነቱ ክፍል በዚህ መልኩ መቀመጡ የተረጋገጠ ቢሆንም ተቀባይነት የለውም ያለው ለሰራተኛው ከሕጉ ከተቀመጠው ጥቅም ያነሰ ያስገኛል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሕጉ ከሕጉ ከተቀመጡት ጥፋቶች ውጪ በሕብረት ስምምነቱ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያስባርሩ ይችላሉ ተብሎ መደንገግ የሚቻል መሆኑን ከማስቀመጡም በላይ በአዋጁ አንቀፅ 134(2) መሰረት የሕብረት ስምምነቱ ለሰራተኛው ሕጉ ካስቀመጠው ጥቅም ያነሰ የሚያስገኝ ሆኖ ከተገኘ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ጥፋትና ጥቅምን በተመለከተ ሕጉ የተለያየ አቋም የያዘ መሆኑን እንጂ አሰሪና ሰራተኛ በሕብረት ስምምነቱ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት በማለት የተስማሙበት ድርጊት ተቀባይነት የለውም የሚለውን ነጥብ አይደለም፡፡ አንድ ሰራተኛ የአሰሪውን ትዕዛዝ ማክበርም ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 13(7) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት መደምደሚያ ህጋዊ መሰረት የሌለው ሲሆን ይግባኝ ሰሚ ቤትም ይህንኑ ሳያርም ማለፉ ተገቢነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፤ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 56547 ሐምሌ 09 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 83500 ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የስራ ውል ያቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከፕሮቪደንት ፈንድ ውጪ የሚከፈላቸው ክፍያ የለም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ